# የስድስተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ የሞዴል ፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች

## ቁጥር አራት

1. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ለጊዜ ስሌት የሚያገለግሉትን ማእዘናዊ ርቀት መለኪያ ( አንግል) እና መስመር ጥምርታን የያዘው የትኛው ነው ?

   ሀ) ኬክሮስ /ተጓዳኝ መስመር　　ሐ) ኬክሮስ / ቋሚ መስመር

   ለ) ኬንትሮስ/ቋሚ መስመር　　መ) ኬንትሮስ /ተጓዳኝ መስመር

2. ከሚከተሉት ውስጥ ስለምስራቅ አፍሪካ አንጻራዊ መገኛ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው ?

   ሀ)ምስራቅ አፍሪካ ከማዕከላዊ አፍሪካ በስተ ምዕራብ ይገኛል

   ለ) ምስራቅ አፍሪካ ከደቡብ አፍሪካ በስተሰሜን ይገኛል

   ሐ) ቀይ ባህር ምስራቅ አፍሪካን በስተሰሜን ያዋስናል

   መ) ህንድ ውቅያኖስ ምስራቅ አፍሪካን በስተምስራቅ ያዋስናል

3. ከሚከተሉት ውስጥ ዐብይ አግዳሚ መስመር ያልሆነው የትኛው ነው ?

   ሀ) የምድር ወገብ　　ሐ) የካንሰር መስመር

   ለ) የካፕሪኮርን መስመር　　መ) ግርንዊች ሜሪዲያን

4. ከምስራቅ አፍሪካ ሃገራት ከህንድ ውቅያኖስ ጋር ረጅም ወሰን ያለው ደሴት ማን ነው ?

   ሀ) ማዳጋስካር　　ሐ) ሞእሽየስ

   ለ)ሲሸልስ　　መ) ኮሞሮስ

5. የምስራቅ አፍሪካ ሰሜናዊ ጫፍ ( 18 ዲግሪ ሰሜን ) የሚገኝበት ሀገር ማን ነው ?

   ሀ) ጂቡቲ　　ለ) ኢትዮጵያ　　ሐ) ማዳጋስካር　　መ) ኤርትራ

6. ከሚከተሉት ምስራቅ አፍሪካን በስተምስራቅ የሚያዋስነው የትኛው ነው ?

   ሀ) ኮንጎ　　ሐ) ቀይ ባህር

   ለ) ህንድ ውቅያኖስ　　መ) ቦትስዋና

7. በመስራቅ አፍሪካ ትልቁ የሆነው የኪሊማንጃሮ ተራራ የት ሃገር ይገኛል?

   ሀ)ታንዛኒያ　　ሐ) ኡጋንዳ

   ለ) ኢትዮጵያ　　መ) ኡጋንዳና ኮንጎ ድንበር

LIVEWORKSHEETS

8. ከሚከተሉት መተግበሪያዎች አንዱ የአንድን ቦታ መገኛ ለማወቅ አያገለግሎ።

ሀ) ጂፒኤስ　　ለ)ፌስቡክ　　ሐ) ጎግል ማፕ　　መ) ጎግል ኧርዝ

9. የካንሰር መስመር የሚግኘው በስንት ዲሪ ላይ ነው ?

ሀ) 23 ½ ሰሜን　　ሐ) 23 ½ ደቡብ

ለ) 66 ½ ደቡብ　　መ) 66 ½ ሰሜን

10. ከሚከተሉት መካከል የምስራቅ አፍሪካ አጎራባች ሃገር ያልሆነው የትኛው ነው ?

ሀ) ሱዳን　　ለ) አንጎላ　　ሐ) ሪፐብሊክ ኮንጎ　　መ) ግብፅ

11. የምስራቅ አፍሪካን በስተምስራቅ በሁል የሚያዋስነው ውሃማ አካል የትኛው ነው ?

ሀ) አትላንቲክ ውቅያኖስ　　ሐ) ቀይ ባህር

ለ) የታስፊክ ውቅያኖስ　　መ) የህንድ ውቅያኖስ

12. ከሚከተሉት መካከል የምስራቅ አፍሪካ ፍጹማዊ መገኛ የሆነው የትኛው ነው ?

ሀ) $18^0$ ሰ እስከ $27^0$ ደ ኬክሮስና $22^0$ እስከ $51^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ

ለ) $3^0$ እስከ $15^0$ ሰ ኬክሮስና $33^0$ እስከ $48^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ

ሐ) $12^0$ እስከ $19^0$ ሰ ኬክሮስና $43^0$ እስከ $44^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ

መ) $12^0$ ሰ እስከ $2^0$ ደ ኬክሮስና $41^0$ እስከ $51^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ

13. ከሚከተሉት ውስጥ የአርክቲክ ክበብ የሚገኘው በየትኛው ንፍቀ ክበብ ነው ?

ሀ) ሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ　　ሐ) ምዕራባዊ ንፍቀ ክበብ

ለ) ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ　　መ) ምስራቃዊ ንፍቀ ክበብ

14. በካርታ ወይም በሉል ላይ ከሰሜን ወደ ደቡብ የተሰመሩ መስመሮች ምን ይባላሉ?

ሀ) የኬክሮስ መስመሮች　　ሐ) የኬንትሮስ መስመሮች

ለ) ቋሚ መስመሮች　　መ) ትይዩ መስመሮች

15. የአንድን አካባቢ ወይም አገር መገኛ ዲግሪን በመጠቀም ማመልከት ምን ይባላል?

ሀ) አካባቢያዊ መገኛ　　ለ) ፍጹማዊ መገኛ

ሐ) አንፃራዊ መገኛ　　መ) ግምታዊ መገኛ

LIVEWORKSHEETS

16. ከሚከተሉት ውስጥ የማላዊን ሃይቅ የሚያዋስኑት ሃገራት የትኞቹ ናቸው?

ሀ) ኬንያ ፣ ዩጋንዳ ፣ ታንዛንያ

ሐ) ሞዛምቢክ ፣ ማላዊ ፣ ታንዛንያ

ለ) ሩዋንዳ ፣ ማላዊ ፣ ቡሩንዲ

መ) ታንዛንያ ፣ ቡሩንዲ ፣ ዛምቤዚ

17. በምስራቅ አፍሪካ ሁለተኛው ትልቁ ተራራ ማን ይባላል ?

ሀ) የኬንያ ተራራ

ሐ) ኪሊማንጃሮ

ለ) ራስ ደጀን

መ) ሜሩ ተራራ

18. ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ ታዋቂ ወንዞች መካከል በታንዛኒያና በሞዛምቢክ ድንበር የሚገኘው የትኛው ነው ?

ሀ) የሩቩማ ወንዝ

ለ) የአዋሽ ወንዝ

ሐ) የ ዐባይ ወንዝ

መ) የዛምቤዚ ወንዝ

19. ምስራቅ አፍሪካን ከሚያዋስኑ ውሃማ አካላት ውስጥ የማይመደበው የትኛው ነው ?

ሀ) ቀይ ባሕር

ሐ) የሕንድ ውቅያኖስ

ለ) የአትላንቲክ ውቅያኖስ

መ) የኤደን ባህረሰላጤ

20. የአንድን ቦታ አቅጣጫ እና የአካባቢን የገበያ ፅር ለመፈለግ የሚጠቅም መተግበሪያ ምን ይባላል?

ሀ) ኮምፒዩተር

ሐ) ጂፒኤስ

ለ) ጎግል ኧርዝ

መ) ጎግል ማፕ

21. ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል የአፍሪካ ቀንድ ሀገር የሆነው የትኛው ነው ?

ሀ) ማዳጋስካር ለ) ታንዛንያ ሐ) ሩዋንዳ መ) ኢትዮጵያ

22. ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ ሃገራት የብዊንዲ ጥቅጥቅ ደን የሚገኘው የት ነው ?

ሀ) ታንዛንያ

ሐ) ኢትዮጵያ

ለ) ዩጋንዳ

መ) ኬንያ

23. ከሚከተሉት ስለ ነጭ የደም ህዋሳት ትክክል የሆነው የትኛው ነው ?

ሀ) ኦክስጅንን በመሸከም ለሰውነታችን ህዋሳት ያደርሳሉ

ለ) ብዙ ደም እንዳይፈስ ለማርጋት ይጠቅማሉ

ሐ) ሄሞግሎቢን አላቸው

መ) ሰውነታችንን ከበሽታ አምጭ ህዋሳት ይከላከላሉ

LIVEWORKSHEETS

24. ከሚከተሉት አማራጮች በኦክስጅን የበለጸገ ደምን ከሳንባ ወደ ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ የሚያስተላልፈው የትኛው ነው ?

ሀ) ፑልሞናሪ ቬይን

ሐ) ትልቁ ደም ቅዳ

ለ) ፑልሞናሪ አርተሪ

መ) ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ

25. ወደ አብይ ትንቧ ለሚገባውና ለሚወታው አየር መተላለፊያ በመሆን የሚያገለግለው የትኛው ነው ?

ሀ) የአየር ከረጢት ለ) ደቂቅ ትንቧ ሐ) ሰርን መ) ድህረ አፍ

26. የስር አተ ትንፈሳ ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ለማውራት

ሐ) ለማሽተት

ለ) በሰውነታችን ውስጥ የሙቀትና ቅዝቃዜን ለማመጣጠን

መ) ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ለህብረ ህዋሶቻችን ማሰራጨት

27. በስር አተ ትንፈሳ አየር ከሰርን በመቀጠል ወደየትኛው የሰውነታችን ክፍል ይሄዳል?

ሀ) የአፍንጫ ቀዳዳ

ሐ) ደቂቅ ትንቧ

ለ) ድህረ አፍ

መ) ተገንጣይ የአየር ቧንቧ

28. ኦክሲጂንን ለመሸከም የሚያስችል ሃመልማል ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ) ፕላትሌትስ ለ) መቅኔ ሐ) ፕላዝማ መ) ሄሞግሎቢን

29. ሰውነታችንን ከበሽታ ለመከላከል የሚጠቅመው የደም ክፍል የትኛው ነው ?

ሀ) ነጭ የደም ሴል

ሐ) ፕላትሌትስ

ለ) ቀይ የደም ሴል

መ) መቅኔ

30. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ፈሳሾችን በድብልቅ ውስጥ ባላቸው የነጥበ ፍሌት ልዩነት የምንለይበት ዘዴ የትኛው ነው ?

ሀ)ቀረራ ለ) ትነት ሐ) ንጥረት መ) ጥሊያ

31. አንድን ነገር ለሁለት ለመክፈል የሚረዳ የቀላል መኪና አይነት ምን ይባላል ?

ሀ) መፈንቅል ለ) መፍቻ ሐ) ሽብልቅ መ) ዘንባይ ወለል

32. ፎቅ ለመውጣት የምንጠቀምበት ደረጃ የምን ምሳሌ ነው ?

ሀ) ሽብልቅ ለ) ዘንባይ ወለል ሐ) መፈንቅል መ) ሽክርክሪት

LIVEWORKSHEETS

33. መዶሻ ከየትኛው ቀላል መኪና አይነት ሊመደብ ይችላል?

ሀ) መፍቻ ለ) ሽብልቅ ሐ) መፈንቅል መ) ሽክርክሪት

34. ድብልቅን ከሚሚ ምንዝሮች የምንለይበት ዘዴ የትኛው ነው ?

ሀ) ንጥረት ለ) ትነት ሐ) ቀረራ መ) ጥሊያ

35. በኮረዳነት ወቅት በሴቶች ላይ ብቻ የሚከሰት ነገር ግን በወንዶች ላይ የማይከሰት ስነ ህይወታዊ ለውጥ የትኛው ነው ?

ሀ) የዳሌ መስፋት ሐ) የድምጽ መጎርነን

ለ) የክብደትና ቁመት መጨመር መ) የጡንቻ መዳበር

36. በአፍ ከመተንፈስ ይልቅ በአፍንጫ መተንፈስ ለምን ተመራጭ ሆነ?

ሀ) አየር በብዛት ስለሚያስገባ ሐ) አየርን አጣርቶና አሙቆ ስለሚያስገባ

ለ) ለመመገቢያነት ስለማያገለግል መ) አየርን ስለሚቀንስ

37. ለኦክስጅንና ለካርቦንዳይ ኦክሳይድ ወደ ደም ውስጥ መግቢያና መውጫ ሆኖ የሚያገለግለው የመተንፈሻ አካል ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ) የአፍንጫ ቀዳዳ ሐ) ሰርን

ለ) ትንከረት ( የአየር ከረጢት) መ) ደቂቅ ትንቧ

38. ከሚከተሉት ልይዘር ድብልቅ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) አየር ለ) የጨው ሙሙት ሐ) ደም መ) ኮካ ኮላ

39. ከሚከተሉት ስለ ታዳሽ ጉልበት ምንጮች ትክክል የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) አካባቢን ይበክላሉ ለ) ነዳጅ የታዳሽ ጉልበት ምንጭ ነው

ለ) ስንጠቀምባቸው ያልቃሉ መ) በቀላሉ ሊተኩ የሚችሉ ናቸው

40. ከሚከተሉት ውስጥ የዘንባይ ወለል ቀላል መኪና አገልግሎት የሆነው የትኛው ነው ?

ሀ) ውሃን ከጉድጓድ ለማውጣት ሐ) ከባድ እቃን መኪና ላይ ለመጫን

ለ) ለመሰርሰሪያነት መ) አንድን ነገር ለሁለት ለመክፈል

LIVEWORKSHEETS

LIVEWORKSHEETS